April 28, 2017

# የሙስሊሙን የትግል ፈለግ የወያኔ ጀሌዎች አይነድፉትም!

ከአንድ ጎጥ ተሰብስበው፣ በመንደር ልጅነት ተደራጅተው፣ በቂም በቀል ተወጥረው በመጡ የጨካኞች ጥርቅም የሚመራው የወያኔ ሥርዓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የበደል ቀንበር ከጫነበት ጊዜ ጀምሮ በተለያየ አቅጣጫ ሕዝቡ ሲታገለው ቆይቷል። አሁንም እየታገለው ነው።

የእስልምና እምነትን መናድንና ሙስሊም ወጣቶችን ከትምህርት ዓለም አስወግዶ ወደመሃይምነት ድቅድቅ ጨለማ ለማስገባት የአገዛዙ ፖሊሲ አድርጎ የዘመተበትን አምባገነን የወያኔን ሥርዓት ሙስሊሙ ህብረተሰብ በተለያየ ሥልት ላለፉት 5 ዓመት እየታገለው ከመሆኑም በላይ ብዙ የሕይወት ዋጋም ከፍሎበታል። ብዙዎችም ታስረዋል፤ በርከት ያሉም ለስደት ተዳርገዋል።

የወያኔ ሥርዓት የሙስሊሞችን የትግል አቅጣጫ ለማስለወጥና ብዥታን ለመፍጠር በመጅሊስና በየመስጊዱ በሰገሰጋቸው ለሆዳቸው ባደሩ ከሃዲዎች አማካይነት ዘርፈ ብዙ ሙከራዎችን አካሂዷል። በእነዚህም ባሥለጠናቸው ካድሬዎች አማካይነት ሙስሊሙ የጀመረውን ሰላማዊ ትግል ወደአምባጓሮና ደም አፍሳሽነት ለመቀልበስ ወያኔ ሰፊ ጥረት አድርጓል። አሁንም እያደረገ ነው።

ወያኔ በአሁኑ ሠዓት አዳዲስ ዘዴዎችን በመቀመር በካድሬዎቹ አማካይነት ለሙስሊሙ መብት የምንታገል ነን የሚሉ የሙስሊም መጠሪያ ስም ያዘሉ ማህበራዊ ድሕረ ገፆችን፣ የኢንተርኔት ሬድዮ ጣቢያዎች እና ዩቲዩቦችን በመፍጥርና በመክፈት ከባድ አደገኛ ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት ላይ ይገኛል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ የሆነው "ሃረከቱል ኢስላሚያ ዳሩልሂጅረተይን ሬድዮ" ብሎ ራሱን የሰየመው ስብስብ በኢትዮጵያ ሰላማዊ ሙስሊሞች ስም ከወደ ሲያትል ዋሽንግተን የወና አፉን የከፈተው የአጥፊዎች ጥርቅም ነው። ይህ የእስልምናን ካባ ደርቦ ከበስተጀርባው በወያኔ ካድሬዎችና አጫፋሪዎች የሚዘወረው ፀረ ሙስሊምና ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ድርጅት በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ መጋለጥና መወገዝ አለበት። የደረበው የማሳሳቻ ካባ በአደባባይ መገፈፍና ወያኔነቱ መሳጣት አለበት።

ይህ ሽብርተኛው "አይሥስ" የተነፈሰበትና ተመሳሳይም ሰንደቅ የሚያውለበልብ ራሱን በአጭሩ "ዲ ኤች ቢ ኤን" (DHBN) ብሎ የሚጠራው የሬድዮ ጣቢያ  በማንኛውም መስፈርት የኢትዮጵያን ሙስሊሞች ሊወክል የማይችልና አሚሮቻችን ከነደፉልን ሰላማዊ የትግል ሥልት ያፈነገጠና ፍፁም ተፃራሪ ጎዳና የያዘ የጥፋት የትግል ሥልት የሚሰብክ ነው። ቀደም ሲል የወያኔ ስርዓት ንፁሃን መሪዎቻችንን ለመወንጀል ፈብርኮ በኢቲቪ የለቀቀውን "ጅሃዳዊ ሃረካት" የተሰኘውን ድራማ ማንም አይረሳውም። የዚህም የሬድዮ ጣቢያ ሃሳቡ የመነጨው ከተመሣሣይ ጭንቅላት ለመሆኑ ማንንም አያደናግርም። በሌላ አነጋገር ይህ የሬድዮ ጣብያ ወያኔ ወያኔ ይሸታል። የወያኔም ግልገል ነው።

ከአሁን ቀደም ክርስቲያንና ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ወያኔ በሃይማኖት ከፋፍሎ ለማፋጀት ያደረጋቸውን ሙከራዎች ሁሉ በጋራ እንዳከሸፍናቸው ሁሉ፣ ይህ ወያኔ በሲያትል ዋሺንግተን በሙስሊም ሬድዮ ጣቢያ ስም የከፈተውን አዲስ የጥቃት ግንባር በጋራ ቅስሙን ሰብረን ከጥቅም ውጭ እንደምናደርገው እምነታችን ጠንካራ ነው።

ይህ ራሱን "ሃረከቱል ኢስላሚያ ዳሩልሂጅረተይን" ብሎ በሙስሊም ስም ተጠልሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ጅሃድ እንዲካሄድ የሚሰብክ የሬድዮ ጣብያ የወያኔ ድርጅት ከመሆን እንደማይዘልና የሚረጨው መርዝ ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰላማዊ ትግልና በአጠቃላይ ለሃገራችን የማይበጅ ስለሆነ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ንቅናቄ ሕብረት ጣቢያውን በጥብቅ ማውገዝ ብቻ



4324 Georgia Avenue NW – Washington, DC 20011 uemm2017@gmail.com

ሳይሆን ከአየር ላይ እንዲወርድ የተቻለውን ጥረትም እንደሚያደርግ ያረጋግጣል። ሌሎች ይህን መዘዘኛ ሬድዮ ጣብያ እንዳያዳምጡና ከአደገኛ መርዙ እንዲጠነቀቁ አደራ ስንል የሚዲያዉንም መስራቾች ከስሕተት ስራችሁ ተወገዱ እንላቸዋለን።

አላሁ አክበር!

የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ንቅናቄ ሕብረት



4324 Georgia Avenue NW – Washington, DC 20011 uempmsg@gmail.com